<u>*AMHARIC*</u>

**ተጨማሪ**

**የሲያትል መንግስታዊ ትምህርት ቤቶች**
**የህዝብ ተሳትፎ ስነ-ስርዓት( ፕሮቶኮል)**

በሲያትል ትምህርት ቤቶች ውስጥ እያንዳንዱ ልጅ ድልን እንዲጐናጸፍ/ድትጐናጸፍ  እድል መስጠት እንደሚገባው እምነታችን ነው። በተጨማሪ ትክክለኛ የሆነ ድጋፍ ከተሰጠ ሁሉም ልጅ ድልን እንደሚቀናጅ እናምናለን።

ለትምህርት ቤቶቻችን ባለን ራእይ ላይ :

- ሁሉም ተማሪዎቻችን በከፍተኛ ደረጃ እንዲጐናጸፉ፣ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለኮሌጅ፣ ለስራና ለህይወታቸው ዝግጁ ሆነው እንዲመረቁ የሚያስፈልጋቸውን  ድጋፍ እንዲያገኙ፤
- ሁሉም ትምህርት ቤት ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ቤት ነው።
- በዋና ጽህፈት ቤት የሚገኙ መሪዎችና ሰራተኞች ለተማሪዎቻችን ልቀትን በአርአያነት(ሚዴል) ያሳያሉ፤
- ኮሚኒቲው በአጠቃላይ ትምህርት ቤቶቻችንን በመደገፍና በማጠናከር ይሳተፋሉ።

ይህንን ራእያችንን በድል ለመወጣት መጠናከር የሚችለው አብዛኛዎቹ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተሳትፎ መሆኑን እንረዳለን። የሲያትል ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች፣ቤተሰቦችና ሌሎች የኮሚኒቲ አባላት ከዲስትሪክት መሪዎች ጋር በተለይ በመላው ዲስትሪክት ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ እንዲነጋገሩ የሚያስችሉ እድሎች እንዲበዙና እንዲሻሻሉ ተግቶ ይሰራል። ለሁሉም ልቀት የተሰኘውን ስትራተጂክ ፕላናችንን ተግባራዊ በምናደርግበት ወቅት፡ ዲስትሪክቱ መቼና እንዴት ኮሚኒቲውን ስለተደረጉት እድገቶች ማሳወቅና በውሳኔ አሰጣጥም ላይ የሚመለከታቸው እንዴትና መቼ እንደሚሳተፉ  በሚመለከት ግልጽ የሆነ አሰራርን መፍጠር እንሻለን።

“ልቀት ለሁሉም” የተሰኘው ፕላናችን የተማሪዎችን ስራ ለማሻሻል ግልጽ የሆኑ የአምስት አመት ግቦችን ነድፏል። እንዲሁም ግቦቻችንን ለመጐናጸፍ ይረዱናል ብለን የምናተኩርባቸውን አምስት መመሪያዎች ይዟል።

1. አካዳሚ — በእያንዳንዱ ክፍል ልቀት እንዲኖር ማረጋገጥ
2. የሰራተኞች አስተዳደር  — በመላው አሰራር ላይ የሚገኙ መሪዎችን ማጠናከር
3. ተቋሞች   — የቲክኖሎጂ አሰራርን ፣ ፋይናንስንና በደንብ የሚሰራ የህንጻ መዋቅርን መገንባት
4. የስራ ክንውን አመራር  — መሳሪያዎችንና አሰራሮችን መፍጠርና ከፍተኛ የስራ ክንውንን ሽልማት የሚሰጥ ባህልን መፍጠር
5. የሚመለከታቸው ተሳትፎ  —ቀንደኛ ከሆኑ ሽርኮቻችን ጋር መነጋገርና በሁሉም ደረጃ እንዲሳተፉ ማድረግ

በእነዚህ በእያንዳንዱ ላይ “ልቀት ለሁሉም” የተሰኘውን በተግባር ለማዋል የሚሰሩ ቡድኖች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሊሳተፉበት የሚችሉበት ለእያንዳንዱ ፕሮግጀት ተገቢ የሆነ ፕላንን ዲዛይን ያደጋል።  ይህንን ሂደት ለመምራት ህዝቡ ሊሳተፍበት የሚችልበትን አሰራር ፡ የአለም እቀፍ ህብረት ህዝባዊ ተሳትፎ ባዘጋጀው መጠን መሰረት ነድፈናል።

*AMHARIC*

**አለም አቀፍ ህብረት ህዝብን ለማሳተፍ የሚያስችሉ ዘርፎች**

| | **ማስታወቅ** | **ማማከር** | **መሳተፍ** | **መተባበር** | **ማጠናከር** |
|---|---|---|---|---|---|
| **የመሳተፍ አላማ** | ሰዎች ችግሮችን፣አማራጮችን፣እድሎችንና /ወይም መፍትሂዎችን እንዲረዱ ሚዛናዊና ተጨባጭ የሆነ መረጃን ማቅረብ | ትንተናዎች፣ አማራጮችን/ወይም ውሳኔዎችን በሚመለከት አስተያየቶችን መቀበል | አሳሳቢ ጉዳዮች ና ተስፋዎች በተከታታይ ግንዛቤና ተቀባይነት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ በሂደቱ ወቅት በቀጥታ ከህዝብ ጋር መስራት | በእያንዳንዱ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ፡ አማራጮችንና መፍትሂዎችን መፈለግን ጨምሮ ከህዝብ ጋር በጋራ መስራት | የመጨረሻውን ውሳኔ በህዝብ እንዲሆን ማድረግ |
| **ለሚመለከታቸው ወገኖች የተሰጠ ተስፋ** | በየጊዜው እናስታውቃችኋለን | በየጊዜው እናስታውቃችኋለን፣ እናዳምጣችኋለን፣ የሚያሳስቧችሁንና ተስፋዎቻችሁን በግምት ውስጥ እናስገባለን ፤ የህዝብ ተሳትፎም በውሳኔዎች ላይ እንዴት ተጽእኖ እንዳመጡ ግብረ መልስን እንሰጣለን። | ህዝቡ የሚያሳስበውንና የሚጠብቃቸው ተስፋዎች አማራጮች በሚፈለጉበት ወቅት መንጸባረቃቸውንና የህዝብ ተሳትፎም በውሳኔዎች ላይ እንዴት ተጽእኖ እናዳመጣ ግብረመልስ መሰጠቱን ለማረጋገጥ እንጥራለን | መፍትሂዎችን በመፈለግ በኩል የህዝብን ምክር እንጠይቃለን፡ ምክሮችንና የቀረቡ ሃሳቦችንም በተቻለ መጠን በውሳኔ ላይ እንጠቀምበታለን | ህዝቡ የሚወስነውን በተግባር ላይ እናውላለን። |
| **ሊያገለግሉ የሚችሉ መሳሪያውች** | - ጭብጦች የያዙ ወረቀቶች<br>- ዌብሳይቶች<br>- የማስተዋወቂያ እለቶች(ኦፕን ሃውስ) | - የህዝብ ስብሰባዎች<br>- መጠይቆች/ጥናቶች | - ዎርክሾፖች<br>- የህዝብን አመለካከት ለማወቅ መጠየቅ | - አማካሪ ኮሚቴዎች<br>- የጋራ ውሳኔዎች | - በድምጽ እንዲወሰን ማድረግ |

*1 በእያንዳንዱ የተሳትፎ ደረጃ የሚገኙ ዝርዝር መሳሪያዎችና ቴክኒኮች ምሳሌዎችን ከዚህ በታች ይገኛሉ።*

*AMHARIC*

**ለሁሉም የትራተጂክ ፕላን ፕሮጀክቶች ለመሳተፍ አሰራራችን/ፕሮቶኮል**
**ለሁሉም ዋና ዋና ፕሮጀክቶች የሲያትል መንግስታዊ ትምህርት ቤት ለሚመለከታችው ሁሉ አመለካከታችንና ሂደታችንን ለማሳወቅ ትጋት ያሳያል።**(“ከላይ ማስታወቅ በሚለው ረድፍ እንደተገለጸው። )

**ሃብቶቻችን በሚፈቅዱልን ግዜ ከሚመለከታቸው ጋር በከፍተኛ ደረጃ ለመሳተፍ እንሞክራለን**( ማማከር፣ መሳተፍ፣መተባበርና ማጠናከር) በጣም ጠቃሚ የሆኑና የሚመለከታቸውን ሊነኩ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን በሚመለከት መሰረታዊ ከሆነው ጥረታችን በላይ ጊዜና ሃብቶች በፈቀዱልን መጠን መረጃን እናካፍላለን።

ከዚህ በታች ያለው ክፍል ፡በተለያየ ደረጃዎች ወቅት በሚደረጉት ተሳትፎዎች ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የሚቀርቡ ተገቢ የሆነ የስራ ተግባራት ምሳሌዎችን ይዟል፤

**ማሳወቅ** : **ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራት በዚህ ደረጃ በሚደረጉት ተሳትፎዎች ወቅት በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ምሳሌዎች ናቸው፤**

*በህዝብ ዌብ ሳይት እንዲወጣ ማድረግ*
• የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ገጽታ፣ ግቦችን ፣ ምእራፎችንና የዚህን ስራ ውጤት ፍላጐት ያላቸው የሚመለከታቸውን ለመድረስ የሚያስችሉ መረጃዎችን መለየት፣
• አብዛኛውን ጊዜ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ፡ ጥያቄዎችና መልሶችን የያዘ የመረጃ ወረቀት። ሊጠየቁ ይችላሉ የተባሉትንና በተሳትፎ ጊዜ የሚከሰቱን የያዘ።
• በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚኖሩትን ደረጃዎች በግልጽ ሊያሳይ የሚችል የጊዜ ሰሌዳና ፡ሃሳብ ለመስጠት እድል የሚሰጡ የጊዜ ገደብን የሚያካትት
• ለጥያቄዎችና አስተያየቶች ሊገናኙት የሚችሉኋቸው ሰራተኞች
• በሂደቱ ጊዜ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች በየጊዜ መኖር
•በየሶስት ወሩ በመላው ዲስትሪክት ስለሚደረጉ ህዝባዊ ስብሰባዎች መረጃ
• ስለ ተጨማሪ የተሳትፎ እድሎች መረጃ

*በርካታ ተጨማሪ የመገናኛ/የመነጋገሪያ ዘዴዎች*
• በቴሌቪዥን የሚተላለፍ የቦርድ ስብሰባዎችና ጠቃሚ ማቴሪያሎችን በዌብሳይት ማውጣት
• በየሶስት ወሩ የሚደረጉ የህዝብ ስብሰባዎች እንዲታወቁ ለማድረግ “ኪድ ሜይል” መጠቀም
• በመላው ዲስትሪክት መታወቅ ያለባቸውን ጠቃሚ ነገሮች የዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ አገልግሎትን በመጠቀም ማሰራጨት
• ተሳትፎን ለማብዛት የዲስትሪክት የአውቶማቲክ መደወያ አሰራሮችን መጠቅም
• ለሰራተኞች፣ቤተሰቦችና ለህዝብ አባላት የኤሌክትሮኒክ የዜና ጽሁፎችን መላክ፡ እያንዳንዳቸው ደግሞ በተራቸው በሚያወጧቸው የዜና ጽሁፎች፡ ስብሰባዎችና ሌሎች መደበኛ የሆኑ የጽሁፍና የቃል መገናኛዎች ሌሎች ቤተሰቦችንና የኮሚኒቲ አባላትን እንዲያስታውቁ ይጠየቃሉ።
    o ለፈረሙ ለሁሉም የሲያትል ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች፣ ወላጆና የኮሚኒቲ አባላት “ስኩል ቢት” የሚለውን ጽሁፍ መላክና በዌብ ሳይት ላይ ማውጣት
    o ክላስሩም ኮኔክሽን የተሰኘውን ለሁሉም አስተማሪዎችና ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች መላክ
    o ፕሪንሲፓል ኮሚኒኬተር የተሰኘውን ለሁሉም ርእሰ መማህራን መላክ
• ቀንደኛ የሆኑ ማስታወቂያዎችና የህዝብ ስብሰባዎችን በሚመለከት በዜና ማስተላለፍ
• ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ጽሁፎች በሲያትል ትምህርት ቤት የዜና ዌብሳይት ላይ ለተጨማሪ መረጃ ደግሞ ወደ ሌላ መረጃ ዌብሳይት የሚመሩ (ሊንክ) እንዲኖራቸው ማድረግ
• በተለይ ተማሪዎችን ለማሳተፍ በየወቅቱ የሚወጡ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም።(የቴክስት ሜሰጆች፣ ዊኪስ ወዘተ,,,)

*የሚሰጡ ሃሳቦችን ለማሰባሰብ ጥረቶች*

- **ለአጠቃላይ ጥያቄዎች ወይም አስተያየቶች መገልገያ የሚሆኑ የኢሜል አድራሻዎች** (goodnews@seattleschools.org)
- **ፕሮጀክቶችን በሚመለከቱ ሃሳቦችን ለመሰብሰብ የተለየ የኤሚል አድራሻዎች** (**ለምሳሌ** capacity@seattleschools.org)
- **ቀንደኛ የሆኑ ፕሮጀክቶችን በሚመለከት ለሰራተኞች ቴሌፎን መደወል ወይም ደብዳቤዎችን መጻፍ**

*አስተያየቶች መድረሳቸውን ማሳወቅና መጠቀም*

- **በየሶስት ወሩ በቅርብ የተሰጡ አስተያየቶችን ጨምሮና በምን መልኩ በግምት ውስጥ እንደገባ ለትምህርት ቤቶች ቦርድ ማሳወቅ በቦርድ ስብሰባዎች ወቅት የቀረቡት ወቅታዊ መረጃዎች በዌብሳይትና በሲያትል ትምህርት ቤቶች ቴሌቪዥን ማስተላለፍ። የቀረቡት ማቴሪያሎች በዌብሳይት ይወጣሉ።**

*መሰናክሎችን መቀነስ*

- **የሲያትል ትምህርት ቤቶች ልዩ ሁኔታ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችና ቤተሰቦች ያለውን መሰናክል በመቀነስ በኩል ይተጋል። ሁሉም የህዝብ ስብሰባ በሚደረግባቸው ቦታዎች አካለ ስንኩላን ለሆኑ እንዲመች ይደረጋል። ዲስትሪክቱ ከቤተሰቦችና ከሰራተኞች ጋር በመሆን አስቀድሞ ለታወቁና ተፈላጊ ለሆኑ ግልጋሎቶች አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል።**
- **የሲያትል ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦቻችንና የኮሚኒቲ አባሎች ለመሳተፍ እንቅፋት የሚሆንባቸውን ለማስወገድ ይተጋል።የሲያትል ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ዋነኛ ቀዳሚ ሃሳቦችን በሚመለከት በየጊዜው የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ያስተረጉማል ወይም ማንኛውም ለቤተሰብ የሚላኩ ደብዳቤዎችን ዋና ዋና በሆኑ ቋንቋዎች ተተርጉመው ለኮሚኒቲ ኣባሎቻችን ይዳረሳሉ። በየሶስት ወሩ በሚደረገው ስብሰባ አስቀድሞ የማስተርጎም አገልግሎትና ሰነዶችን መተርጎምን በሚመለከት እንዲታወቅ ይደረጋል።**

*ህዝብን መድረስ*

- **የፕሮጀክቶች ማናጀሮች ከባይሊንጓል ቤተሰብና ኮሚኒቲ ተሳታፊ ሰራተኛ ጋር ቅንጅትን ፈጥረው ይፋና ይፋ ያልሆነ የኮሚኒቲ መገናኛ(ኔትዎርክ) በመፍጠር በተሳካ ሁኔታ በትምህርት ቤቶቻችን የሚማሩ የተለያዩ ህዝቦችን መድረስ ። ይህንን የህዝብ መድረስ ጥረት ስኬታማ እንዲሆን ለመደገፍ መረጃዎችን በሰአቱ ለማካፈል እንጥራለን።**

**ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አሰራሮች ዲስትሪክቱ የፕሮጀክቶች ጠቃሚነት ከፍ በሚልበት ወቅትና መረጃን ከማካፈል በላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት ሃብቶች በሚፈቅዱትና መሰረት ዲስትሪክቱ ከሚያከናውናቸው የስራ ድርጊቶች ውስጥ ለምሳሌ የቀረቡ ናቸው።**

**ማማከር: ከላይ የተገለጹት ተግባራት በዚህ ደረጃ ለሚደረጉ ተሳትፎዎች ሊሆኑ የሚችሉ ተግባራት ናቸው፥ በተጨማሪም፤፡**

*በህዝብ የዌብሳይት ላይ እንዲወጡ ማድረግ*

- **ጉዳይ ከሚመለከታቸው ቡድኖችና አማካሪ ኮሚቴዎች ጋር የተዘገበ የሁለት-ወገን ግንኙነት ማድረግ**

*የተለያየ አይነት ኮሚኒኬሽን*

- **ህዝብን በስብሰባ ለማሳተፍና በጣም አሳሳቢ የሆነ መረጃን ለመለዋወጥ “ ኪድ ሜይል” እና በቀጥታ ደብዳቤዎችንና ፓስት ካርዶችን መላክ**
- **ተሳትፎን ለማብዛት የዲስትሪክቱን የአውቶማቲክ የመደወያ አሰራር መጠቀም**

## AMHARIC

*ሃሳቦችን ለማሰባሰብ የሚደረጉ ጥረቶች*

• በትንተናዎችን፣ አማራጮችና ውሳኔዎችን ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችን በሚመለከት የሚያሳስቡና ተስፋ በተጣለባቸው ላይ የህዝብን አስተያየት መሰብሰብ
• የህዝብ ስብሰባዎች/ ገለጻዎች/የቡድን ውይይቶች/የተለያዩ አመለካከቶች የሚወክሉ ክስተቶች በእኩልነት እንዲወከሉ ማድረግ
• በሬዲዮና በቴሌቪዥን መድረኮች በመሳተፍ መረጃዎችን ማካፈልና ከኮሚኒቲ አባላት መስማት
• በዌብሳይት ሃሳብ መለዋወጥ

*የተሰጡ ሃሳቦች መድረሳቸውንና በጥቅም ላይ መዋላቸውን ማስታወቅ*

• ሱፐርኢንተንዳንቷ ለትምህርት ቤት ቦርድ ያቀረበችውን ወቅታዊ መሻሻሎችን በጽሁፍ ማቅረብ

**መሳተፍ : ከላይ የተገለጹት ሁሉም ተግባሮች በዚህ ደረጃ ለሚደረጉት ተሳትፎዎች ሊሆኑ የሚችሉ ተግባሮች ናቸው ፡ በተጨማሪም ፡**

*በህዝብ የዌብ ሳይት ማውጣት*

• ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በህዝብ የቀረቡት አስተያየቶች መጻፍና በምን መልኩ በግምት ውስጥ እንደገባ የተሰጠውን መልስ ማስታወቅ
• ሃሳቦችንና/ወይም ውሳኔዎችን የሚሰጡ የኮሚቴ አባላት ስሞች፣ ጽህፈት ቤቶችና የመገናኛ መረጃዎች

*አስተያየትን ለማግኘት ጥረት ማድረግ*

• ያለቀጠሮ የሚደረጉ ስብሰባዎች/ ውሳኔ ከሚሰጡት ጋር የተደረጉ ጊዜ የወሰዱ ንግግሮች ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ዎርክሾፖችን ማድረግ
• ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር የትኩረት ቡድኖች

*የተሰጡ ሃሳቦች መድረሳቸውና በጥቅም ላይ መዋላቸውን ማስታወቅ*

• የቀረቡ ሃሳቦችና ለቀረቡትም ሃሳቦች የተሰጣቸውን መልሶች በከፍተኛ ደረጃ ጭማቂያቸውን ማቅረብ

**መተባበር : ሁሉም ከላይ የተገለጹት ተግባሮች በዚህ ደረጃ ለሚደረጉ ተሳትፎዎች ሊውሉ የሚችሉ ናቸው። በተጨማሪም፤**

*አስተያየቶችን ለመሰብሰብ የሚደረጉ ጥረቶች*

• ውሳኔዎችንና ሃሳቦችን በሚሰጡ ኮሚቴዎች ውስጥ የህዝብን አባላት መጨመር
• በዲስትሪክት ሰራተኞችና ጉዳዩ በሚመለከታቸው መካከል ለውሳኔዎችና በተግባር ላይ ለማዋል የጋራ ሃላፊነት
• ክስተቶችና ቀዳሚ ሃሳቦች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በጋራ መንደፍና/ወይም ማዘጋጀት

*የሚሰጡ ሃሳቦች መድረሳቸውና በተግባር ላይ መዋላቸውን ማስታወቅ*

• የቀረቡ ሃሳቦችና በውሳኔ ላይ እንዴት በተግባር ላይ እንደሚውሉ ዝርዝር የሆነ ማጠቃለያ